# ምነው ፣ ድምጹ ጠፋ ?

ችጋር የጠበሰው ፣ ያባረረው ጠኔ
ደደቢት ያደገ ፣ መርዛም ፣ ጊንጥ ወያኔ
የአረብ ቡችላ ፣ የባዕድ ምስለኔ
አገር ፣ ሸቀጥ ሆነች ፣ በዚህ አረመኔ
አያመጣው የለ ፣ ጉድ አሳየኝ አይኔ ።

በግራም በቀኙም ፣ አገር ተቆራርሳ
እየሸነሸነ ፣ ሲሸጥ ፣ እያነሳ
ለቻይና ለህንዱ ፣ ቸርችሯት በቤሳ
በህንድና በአረብ ፣ ተቆፍራ ታርሳ
ዜጋ እየተራበ ፣ መጤው እያገሳ
ዘብ ፣ ጠባቂ ጠፍቶ ፣ ቀጭጫ ኮስሳ
ባዕድ ሲሻማባት ፣ እንዳሻው ሲያነሳ
እናቱ ስትሞት ፣ በችጋር ተጠብሳ
ጀግናው ፣ የት ደረሰ ፣ መሳሪያ አያነሳ?

አለች ፣ ብሎ እንዳይል ፣ ከመቃብር ቆማ
ሞተች ፣ ብሎ አያለቅስ ፣ ጣሯን እየሰማ
ጉልበት አላነሰው ፣ አይደለ ደካማ
መታደግ ሲቻለው ፣ እናት ሀገር ፣ ታማ
ወይኔ ! ምን ፋይዳ ፣ አለው ፣ ከንቱ ቁጭትማ
ባዕድም ይችላል ፣ ከንፈር መምጠጥማ ።

በሹምባሽ ፣ ምስለኔ ፣ መአት ሲዘንብባት
አረመጥ ላይ ፣ ጥለው ፣ እሳት ሲያነዱባት
የእንግዴ ልጅ ፣ ባንዶች እየቀለዱባት
መጤው ፣ በዜጋ ላይ ፣ አዛዥ ሲሆንባት
አምርታ እየሰጠች ፣ እሷን እየራባት
እስክትሞት ፣ ነው ወይ ፣ ቆሞ የሚታዘባት
ምነው ፣ ድምጹ ጠፋ ፣ ልጇ ፣ የት ቀረባት
ለመቼ ፣ ሊሆን ነው ፣ ለችግር ያልረባት ።

ታዛቢው ... November 16/2011

EthioLion.Com